# የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የባሕላዊ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን

**በጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ ቁጥር 2200 A (xxxi) እ.ኤ.አ. ዲሴምበር 16 ቀን 1966 ፀድቆ አባል ሀገራት እንዲያፀድቁት እና እንዲቀበሉት የቀረበ**

**ሥራ ላይ የዋለበት ዕለት፡- በአንቀጽ 27 መሰረት እ.ኤ.አ. ጃንዋሪ 3 ቀን 1976**

## መግቢያ

**የዚህ ቃል ኪዳን አካል የሆኑ ሀገራት**

በተባበሩት መንግሥታት ቻርተር በታወጁት መርሆዎች መሰረት የሰው ዘር በሙሉ አብሯቸው የተፈጠረ ክብር ያላቸው መሆኑን፣ እኩል እና ከስብእናቸው ሊነጠሉ የማይችሉ መብቶች ያሏቸው መሆኑን አውቆ መቀበል ለነፃነት፣ ለፍትሕና ለዓለም ሰላም መሰረት መሆኑን በመገንዘብ፤

እነዚህ መብቶች ሰው በተፈጥሮ ከተጎናፀፈው ክብር የሚመነጩ መሆናቸውን በማወቅ፤

በሰብአዊ መብቶች ዓለም አቀፍ መግለጫ መሰረት ሰዎች ከፍርሃትና ከድህነት ነፃ ሆነው የሚኖሩበት ሁነኛው ዓለም ሊፈጠር የሚችለው እያንዳንዱ ሰው የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊ እና የባሕላዊ መብቶቹን፤ እንዲሁም የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶቹን ለመቀዳጀት የሚያስችለው ሁኔታዎች ሲፈጠሩለት ብቻ መሆኑን በማወቅ፤

ሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶች በመላው ዓለም እንዲከበሩና እንዲጠበቁ ለማድረግ በተባበሩት መንግሥታት ቻርተር መሰረት ሀገራት ያለባቸውን ግዴታ በመገንዘብ፤

ግለሰቡም ለሌሎች ግለሰቦችና ለሚኖርበት ሕብረተሰብ ኃላፊነት ስለአለበት፤ በዚህ ቃል ኪዳን የተደነገጉት መብቶች እንዲከበሩና እንዲጠበቁ የበኩሉን ጥረት ማድረግ ያለበት መሆኑን በመረዳት፣ በሚከተሉት አንቀጾች ላይ ተስማምተዋል፡፡

# ክፍል አንድ

## አንቀጽ 1

1. ሁሉም ሕዝቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት አላቸው፡፡ ይህን መብት በመገናፀፋቸው የፖለቲካ ህልውናቸውን በነፃነት የመወሰን፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ባሕላዊ ዕድገታቸውንም በነፃነት የማራመድ መብት አላቸው፡፡
2. ሁሉም ሕዝቦች በጋራ ጥቅም መርሆ ላይ የተመሰረተ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ትብብር ግዴታቸውንና ዓለም አቀፍ ሕግን ሳይጥሱ የተፈጥሮ ሀብታቸውን ለራሳቸው ጉዳይ በነፃነት መጠቀም ይችላሉ፡፡ በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን አንድ ሕዝብ ለኑሮው አስፈላጊ የሆኑትን የራሱን ጥቅሞች አይነፈግም፡፡
3. ራሳቸውን ለማያስተዳድሩና በሞግዚት ለሚተዳደሩ ግዛቶች የማስተዳደር ኃላፊነት ያለባቸው ሀገራትን ጨምሮ፣ የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ ሀገራት ሁሉ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ከተባበሩት መንግሥታት ቻርተር ድንጋጌ ጋር በሚጣጣም ሁኔታ ተግባራዊ እንዲሆን ይጥራሉ፤ ይህንን መብት ያከብራሉ፡፡

# ክፍል ሁለት

## አንቀጽ 2

1. እያንዳንዱ የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ ሀገር በግሉ እና በተለይ ደግሞ ኢኮኖሚያዊ እና ቴክኒካዊ ድጋፍ በታከለበት ዓለም አቀፍ እርዳታ እና ትብብር አማካኝነት በእጁ የሚገኙትን ሀብቶች አሟጦ በመጠቀም፤ በዚህ ቃል ኪዳን ዕውቅና ያገኙት መብቶች ቀስ በቀስ በሙሉ ተግባራዊ እንዲሆኑ ሕግ ማውጣትን ጨምሮ ማናቸውንም ተገቢ እርምጃዎች ለመውሰድ ተስማምተዋል፡፡
2. የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ ሀገራት በዘር፣ በቀለም፣ በፆታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ ወይም በሌላ አስተሳሰብ፣ በብሔራዊ ወይንም በማኅበራዊ አመጣጥ መነሻነት በሀብት፣ በትውልድ ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ምንም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ በዚህ ቃል ኪዳን የተደነገጉትን መብቶች ለማስከበር ተስማምተዋል፡፡
3. በመልማት ላይ ያሉ ሀገራት ሰብአዊ መብቶችንና ሀገራዊ ኢኮኖሚያቸውን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ዜጎቻቸው ያልሆኑ ሰዎች በዚህ ቃል ኪዳን ዕውቅና ባገኙት የኢኮኖሚ መብቶች ተጠቃሚ የሚሆኑበት ደረጃ ሊወስኑ ይችላሉ፡፡

## አንቀጽ 3

የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ ሀገራት ወንዶችና ሴቶች በቃል ኪዳኑ በተደነገጉት ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ባሕላዊ መብቶች እኩል ተጠቃሚ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተስማምተዋል፡፡

## አንቀጽ 4

አንድ ሀገር ይህንን ቃል ኪዳን ተከትሎ በሚደነግጋቸው መብቶች አጠቃቀም ላይ ከመብቶቹ ባሕርይ ጋር በሚስማማ መልክ በሕግ በተወሰነው መሰረት ብቻና በዴሞክራሲያዊ ሕብረተሰብ የጠቅላላውን ጥቅም ለመንከባከብ ሲባል ብቻ ገደብ ለመጣል ያለውን መብት የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ ሀገራት ይቀበላሉ፡፡

## አንቀጽ 5

1. በዚህ ቃል ኪዳን የተጠቀሰ ማንኛውም ድንጋጌ ማንኛውም ሀገር፣ ቡድን ወይም ግለሰብ በቃል ኪዳኑ የተደነገጉትን ማናቸውንም መብቶችና ነፃነቶች ለመግፈፍ ወይም በቃል ኪዳኑ ከተደነገገው በበለጠ ሁኔታ ለመገደብ የታቀደ ድርጊት ለመፈፀም የሚያስችል መብት እንዳለው ተደርጎ ሊተረጎም አይችልም፡፡
2. በየትኛውም ሀገር በሕግ፣ በስምምነት፣ በደንብ ወይም በልማድ ተቀባይነት ያገኙትን መሰረታዊ ሰብአዊ መብቶች ይህ ቃል ኪዳን ዕውቅና አይሰጣቸውም ወይም እኩል አያያቸውም በሚል ሰበብ መገደብ ወይም መሻረር አይፈቀድም፡፡

# ክፍል ሦስት

## አንቀጽ 6

1. የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ ሀገራት የመሥራት መብትን ተቀብለዋል፡፡ ይህ መብት ማንኛውም ሰው በነፃ ፈቃዱ የመረጠውን ወይም የተቀበለውን ሥራ ሠርቶ ሕይወቱን ለመምራት የሚያስችል የተመቻቸ ሁኔታ መፍጠርን የሚጨምር ሆኖ የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ ሀገራት ይህን መብት ለማስከበርም ተገቢውን እርምጃ ይወስዳሉ፡፡
2. የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ ሀገር ይህን መብት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ የሚወስዳቸው እርምጃዎች፣ ለግለሰቡ መሰረታዊ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ነፃነቶቹን በሚያስጠብቁ ሁኔታዎች ቀጣይነት ያለው ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ባሕላዊ ዕድገትን የሚያስገኙና ምርታማ የሥራ ዕድል የሚፈጥሩ የቴክኒክ፣ የሙያ አመራርን የስልጠና ፕሮግራሞችን፣ ዘዴዎችንና ፖሊሲዎችን መንደፍን የሚያካትት መሆን ይኖርበታል፡፡

## አንቀጽ 7

የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ ሀገራት እያንዳንዱ ሰው በተለይ የሚከተሉትን የሚያረጋግጥ ፍትሐዊና አመቺ የሥሥራ ሁኔታ የማግኘት መብት እንዳለው ተቀብለዋል፡፡

ሀ/ ለሁሉም ሠራተኞች የሚሰጥ ክፍያ ቢያንስ፡-

1. ምንም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ እኩል ዋጋ ላለው ሥሥራ ተገቢ እና እኩል ክፍያ፣ በተለይ ሴቶች ወንዶች ከሚሰሩበት ባላነሰ የሥሥራ ሁኔታ ውስጥ መሥሥራታቸውና ለእኩል ሥሥራ እኩል ክፍያ የሚያገኙ መሆኑን፤
2. በዚህ ቃል ኪዳን ድንጋጌዎች መሰረት ራሳቸውንም ሆነ ቤተሰቦቻቸውን በደህና ሁኔታ ለማኖር የሚያስችል ክፍያ የሚያገኙ መሆኑን፤

ለ/ ከአደጋ ነፃ የሆነና ጤናማ የሥራ ሁኔታ፤

ሐ/ ከአገልግሎት ዘመንና ከችሎታ በስተቀር ሌሎች መመዘኛዎች ከግምት ውስጥ ባለማስገባት እያንዳንዱ ሠራተኛ በተቀጠረበት ሥራ ከፍ ወዳለ ደረጃ ለማደግ እኩል ዕድል ማግኘቱን፤

መ/ ዕረፍት፣ የመዝናኛ ጊዜና ተገቢ የሆነ የሥራ ሰዓቶች ገደብ፣ በተወሰኑ ወቅቶች ከክፍያ ጋር የሚሰጥ ፈቃድ፣ እንዲሁም ለሕዝብ በዓላት የሚሰጥ ክፍያ ማግኘቱን፤

## አንቀጽ 8

1. የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ ሀገራት የሚከተሉትን መብቶች ለማስከበር ተስማምተዋል፡፡

ሀ/ ማንኛውም ሠራተኛ ኢኮኖሚያዊና ማኀበራዊ ጥቅሞቹን ለማስጠበቅ የሠራተኛ ማኀበራትን ለማቋቋምና የሚመለከተው ማኀበር ደንቦች እስከፈቀዱ ድረስ የመረጠው ማኀበር አባል የመሆን መብት አለው፡፡ በሕግ ከተደነገገውና በዴሞክራሲያዊ ሕብረተሰብ ብሔራዊ ፀጥታን ወይም የሕዝብን ሰላም ወይም የሌሎች መብትና ነፃነት ለማስከበር አስፈላጊ ከሆነው በስተቀር ምንም ዓይነት ገደብ አይደረግበትም፡፡

ለ/ የሠራተኞች ማኀበራት ብሔራዊ ፌዴሬሽኖችን ወይም ኮንፌዴሬሽኖች የመመስረት መብት አላቸው፤ ኮንፌዴሬሽኖቹም ዓለም አቀፍ የሠራተኛ ማኀበራት ድርጅቶችን የመመስረት ወይም አባል የመሆን መብት አላቸው፡፡

ሐ/ በሕግ ከተደነገገውና በዴሞክራሲያዊ ሕብረተሰብ ብሔራዊ ፀጥታን፣ የሕዝብ ሰላም ወይም የሌሎችን መብትና ነፃነት ለማስከበር አስፈላጊ ከሆነው በስተቀር የሠራተኞች ማኀበራት ምንም ዓይነት ሌላ ገደብ ሳይደረግባቸው በነፃነት የመንቀሳቀስ መብት አላቸው፡፡

መ/ በሚመለከተው ሀገር ሕግ መሰረት የሚከናወን ሥራ የማቆም አድማ መብት ይከበራል፡፡

2. ይህ አንቀጽ የጦር ኃይል ወይም የፖሊስ አባላት ወይም የመንግሥት አስተዳደር ሠራተኞች በእነዚህ መብቶች ስለሚጠቀሙበት ሁኔታ ላይ ሕጋዊ ገደቦች ማድረግን አይከለክልም፡፡
3. በነፃ መደራጀትንና የመደራጀት መብትን ለማስከበር እ.ኤ.አ በ1948 የተደረገው ዓለም አቀፍ የሥራ ድርጅት ስምምነት ፈራሚ ሀገራት በዚህ ስምምነት የተረጋገጡትን የመብት ዋስትናዎች የሚፃረር ሕግ እንዲደነግጉ ወይም ዋስትናዎቹን ሊፃረር በሚችል መልክ ሕጉን ሥራ ላይ እንዲያውሉ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ አይፈቅድላቸውም፡፡

## አንቀጽ 9

የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ ሀገራት ማንኛውም ሰው ማኅበራዊ መድንን ጨምሮ ማኅበራዊ ዋስትና የማግኘት መብት ያለው መሆኑን ተቀብለዋል፡፡

## አንቀጽ 10

**የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ ሀገራት የሚከተሉትን ተቀብለዋል፤**

1. ቤተሰብ የሕብረተሰብ መሰረት በመሆኑ በተለይ በሚመሰረትበት ጊዜና ለልጆች አስተዳደግና ትምህርት ኃላፊነትን በሚሸከምበት ጊዜ አቅም በፈቀደ መጠን ከሁሉም የሰፋ ጥበቃና ድጋፍ ሊሰጠው ይገባል፡፡ ጋብቻም በተጋቢዎቹ ፈቃድ የሚመሰረት ይሆናል፡፡
2. ለእናቶች ከወሊድ በፊትና በኂላ በቂ ለሆነ ጊዜ እንክብካቤ መደረግ አለበት፡፡ በዚህ ጊዜም ለሚሰሩ እናቶች ከደመወዝ ጋር ወይም ከበቂ የማኅበራዊ ዋስትና ጥቅሞች ጋር ፈቃድ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡
3. በወላጆቻቸው ወይም በሌላ ምክንያት ምንም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ ለሕፃናት እና አካለ መጠን ላልደረሱ ወጣቶች ልዩ ጥበቃና ድጋፍ የሚሹ እርምጃዎች ሊወሰዱ ይገባል፡፡ ሕፃናት እና ወጣቶች ከኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ብዝበዛ መጠበቅ አለባቸው፡፡ ለሥነ ምግባራቸው ወይም ለጤንነታቸው ጎጂ ወይም ለሕይወታቸው አደገኛ በሆነ ወይም የተፈጥሮ ዕድገታቸውን በሚያሰናክል ሥራ ላይ እንዲሰማሩ ማድረግ በሕግ የሚያስቀጣ ሊሆን ይገባል፡፡ እንዲሁም ለጋ ሕፃናትን በደመወዝ ቀጥሮ ማሰራት የሚከለከልበትንና የሚያስቀጣበትን ዝቅተኛ የዕድሜ ገደብ ሀገራት መወሰን አለባቸው፡፡

## አንቀጽ 11

1. የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ ሀገራት ማንኛውም ሰው በቂ ምግብ፣ ልብስና መኖሪያ ቤትን ጨምሮ ለራሱና ለቤተሰቡ በቂ በሆነ የኑሮ ደረጃ ለመኖርና የኑሮውን ሁኔታ ለማሻሻል መብት ያለው

መሆኑን ያውቃሉ። አባል አገሮቹ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ዓለም አቀፍ ትብብርን አስፈላጊነት ተገንዝበው የዚህን መብት ተግባራዊነት ለማረጋገጥ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳሉ።

2. የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ ሀገራት ማንኛውም ሰው ሳይራብ ለመኖር ያለውን መሰረታዊ መብት በመገንዘብ በተናጠልም ሆነ በዓለም አቀፍ ትብብር አማካይነት የሚከተሉትን ለማሳካት ዝርዝር መርኃ ግብርን ጨምሮ አስፈላጊ እርምጃዎችን ይወስዳሉ፤

   ሀ/ ቴክኒካዊና ሳይንሳዊ ዕውቀትን በመጠቀም የምግብ አመራረት፣ ክምችትና ስርጭት ዘዴን ለማሻሻል፣ የአልሚ ምግብ መሰረታዊ ዕውቀቶች ለማሰራጨት፣ እጅግ የተመጣጠነ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም እንዲኖር የግብርና ስርዓቱን ማሻሻል፤

   ለ/ ምግብ አስመጪና ላኪ ሀገራት የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ግምት ውስጥ በማስገባት በፍላጎታቸው መሰረት የተመጣጠነ የዓለም የምግብ አቅርቦት ስርጭት እንዲኖር ለማረጋገጥ፤

## አንቀጽ 12

1. የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ ሀገራት ማንኛውም ሰው ሊደረስበት ወደሚችል ከፍተኛ የአካልና የአእምሮ ጤንነት ወደ ተሟላበት የኑሮ ደረጃ የመድረስ መብት ያለው መሆኑን ያውቃሉ።
2. ይህን መብት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ የቃል ኪዳኑ ተዋዋይ ሀገራት የሚወስዱት እርምጃዎች የሚከተሉትን ማካተት አለባቸው፡-

   ሀ/ ሞተው የሚወለዱትንና ከተወለዱ በኋላ የሚሞቱትን ሕፃናት ቁጥር መቀነስ እና የሕፃናት ጤና ዕድገት ማመቻቸት፤

   ለ/ የአካባቢና የኢንዱስትሪን ንጽሕና አጠባበቅ ማሻሻል፤

   ሐ/ ወረርሽኝን፣ አካባቢያዊና ከሥራ ጋር የተዛመዱ በሽታዎችን መከላከል፣ ማከምና መቆጣጠር፤

   መ/ ሰዎች ሲታመሙ የሕክምና አገልግሎትና እንክብካቤ የሚያገኙበትን አስፈላጊ ሁኔታ ማመቻቸት።

## አንቀጽ 13

1. የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ ሀገራት ማንኛውም ሰው ትምህርት የማግኘት መብት ያለው መሆኑን ያውቃሉ። ትምህርት የሰውን ስብእናና የክቡርነት ስሜት ሙሉ በሙሉ ለማሳደግ በሚያስችል አቅጣጫ መመራት እንዳለበትና ለሰብአዊ መብቶችና መሰረታዊ ነፃነቶች የሚሰጠውን ከበሬታ የሚያጠናክር መሆን እንዳለበትም ተስማምተዋል። ትምህርት ማንኛውም ሰው በነፃ ሕብረተሰብ ውስጥ ፍሬያማ ተሳትፎ እንዲኖረው የሚያስችል፣ በሁሉም ሀገራት፣ ዘሮች፣ ጎሳዎች ወይም የሃይማኖት ክፍሎች መካከል መግባባትን፣ መቻቻልንና ወዳጅነትን

የሚያጠናክርና የተባበሩት መንግሥታትን የሰላም ጥበቃ እንቅስቃሴዎች የሚያግዝ እንዲሆን ተስማምተዋል፡፡

2. የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ ሀገራት ይህ መብት ሙሉ ለሙሉ እንዲረጋገጥ ለሚከተሉት ዕውቅና ይሰጣሉ፤

   ሀ/ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት መማር ለሁሉም ግዴታ ሆኖ ትምህርቱም በነፃ የሚሰጥ ይሆናል፡፡

   ለ/ የቴክኒክና የሙያ ትምህርትን ጨምሮ በማናቸውም ተስማሚ በሆኑ ዘዴዎች በተለያየ መልኩ የሚሰጠው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በአጠቃላይ ለሁሉም ክፍት እና የሚዳረስ ይሆናል፤ ትምህርቱም ደረጃ በደረጃ በነፃ እንዲሰጥ ይደረጋል፤

   ሐ/ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ችሎታን መሰረት በማድረግ በማንኛውም አመቺ ዘዴ ለሁሉም ይዳረሳል፤ ትምህርቱም በሂደት በነፃ እንዲሰጥ ይደረጋል፤

   መ/ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን ያልተማሩ ወይም ያላጠናቀቁ ሰዎች በተቻለ መጠን መሰረታዊ ትምህርት እንዲከታተሉ ይበረታታሉ፤ ትምህርቱም በስፋት እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡

   ሠ/ ትምህርት ቤቶችን በየደረጃው የማስፋፋት ያልተቆጠበ ጥረት ይደረጋል፤ ብቃት ያለው የነፃ ትምህርት ሥርዓት ይመሰረታል፤ የመምህራን የኑሮ ሁኔታም ያለማቋረጥ ይሻሻላል፡፡

3. የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ ሀገራት ወላጆችና እንደነገሩ ሁኔታ ሕጋዊ ሞግዚቶች፣ መንግሥት ካወጣው መሰረታዊ የጥራት መመዘኛ የሚያንስ እስካልሆነ ድረስ በማንኛውም ትምህርት ቤት ልጆቻቸውን የማስተማር እንደየእምነታቸውም የሃይማኖትና የግብረገብ ትምህርት እንዲማሩ የማድረግ መብታቸውን ለማክበር ተስማምተዋል፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሱት መርሆዎች እስከተጠበቁና በትምህርት ተቋሙ የሚሰጠው ትምህርት መንግሥት የወሰነውን መሰረታዊ የትምህርት ጥራት መመዘኛ እስካሟላ ድረስ የዚህ አንቀጽ ማናቸውም ክፍል ግለሰቦችና ሌሎች አካላት የትምህርት ተቋማት ለመመስረትና ለመምራት ባላቸው ነፃነት ውስጥ ጣልቃ ለመግባት እንደሚያስችል ተደርጎ ሊተረጎም አይችልም፡፡

## አንቀጽ 14

የዚህ ቃል ኪዳን እያንዳንዱ ተዋዋይ ሀገር የቃል ኪዳኑ አባል በሆነበት ጊዜ ግዛቱ በሆነ ከተማ ወይም በሌሎች ግዛቶቹ ውስጥ ከክፍያ ነፃ የሆነ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት በግዴታ መስጠት አልቻለ እንደሆነ፤ ይህን ለሁሉም ሰዎች ከክፍያ ነፃ የሆነ ትምህርት በግዴታ የሚሰጥበትን መርህ በተወሰኑ ዓመታት ውስጥ ደረጃ በደረጃ በሥራ ለመተርጎም የሚያስችል ዝርዝር የሥራ ዕቅድ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ አዘጋጅቶ ያፀድቃል፡፡

## አንቀጽ 15

1. የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ ሀገራት ማንኛውም ሰው፤

   ሀ/ በባሕላዊ እንቅስቃሴዎች የመሳተፍ፤

   ለ/ ሳይንሳዊ ዕድገት በሚያስገኛቸው ጥቅሞች የመጠቀም፤

   ሐ/ ፈጣሪ ለሆነባቸው የሳይንስ፣ የሥነ ጽሑፍ ወይም የስነ ጥበብ ውጤቶች መንፈሳዊና ቁሳዊ ጥቅም የማግኘት መብት ያለው መሆኑን ያውቃሉ፡፡

2. ይህን መብት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ በቃል ኪዳኑ ተዋዋይ ሀገራት የሚወሰዱ እርምጃዎች ሳይንስንና ባሕልን ለመንከባከብ፣ ለማሳደግና ለማስፋፋት የሚያስፈልጉ እርምጃዎችን ይጨምራሉ፡፡

3. የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ ሀገራት ለሳይንሳዊ ምርመራና ለፈጠራ ሥራ አስፈላጊ የሆነውን ነፃነት ለማክበር ተስማምተዋል፡፡

4. የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ ሀገራት በሳይንስና ባሕል መስኮች የዓለም አቀፍ ግንኙነቶችንና ትብብሮችን በማበረታታትና በማሳደግ የሚገኘውን ጥቅም ይገነዘባሉ፡፡

# ክፍል አራት

## አንቀጽ 16

1. የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ ሀገራት ስለወሰዷቸው እርምጃዎችና በቃል ኪዳኑ ዕውቅና ያገኙትን መብቶች በማስከበሩ ረገድ ስለተገኘው ውጤት በዚህ የቃል ኪዳኑ ክፍል በተደነገገው መሰረት ዘገባ ያቀርባሉ፡፡

2. ሀ/ ሁሉም ዘገባዎች ለተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ መቅረብ አለባቸው፤ ዋና ጸሐፊውም የቀረቡለትን ዘገባዎች ቅጂዎች በዚህ ቃል ኪዳን በተደነገገው መሰረት እንዲመረመሩ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ጉዳዮች ምክር ቤት ያቀርባል፡፡

   ለ/ የተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ በዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ ሀገራት የቀረቡለትን የዘገባዎች ቅጂዎች ወይም የዘገባዎቹን የተወሰኑ ክፍሎች እነዚሁ ሀገራት አባል ለሆኑባቸውና ልዩ ተልዕኮ ለተሰጣቸው ድርጅቶች ያስተላልፋል፡፡ ዋና ጸሐፊው የዘገባዎቹን ቅጂዎች ወይም የተወሰኑትን ክፍሎች ለእነዚህ ድርጅቶች የሚያስተላልፈው በመተዳደሪያ ደንባቸው መሰረት ጉዳዩ የሚመለከታቸው ከሆነ ነው፡፡

## አንቀጽ 17

1. የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ጉዳዮች ምክር ቤት ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ልዩ ተልዕኮ የተሰጣቸው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅቶችንና የዚህን ቃል ኪዳን ተዋዋይ ሀገራትን አማክሮ በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ይህ ቃል ኪዳን ሥራ ላይ በዋለ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ተዋዋይ ሀገራት በሚወሰንላቸው ቅደም ተከተል ዘገባቸውን ያቀርባሉ፡፡
2. ዘገባዎቹ በዚህ ቃል ኪዳን ውስጥ የተደነገጉትን ግዴታዎች በመፈፀም በኩል ያጋጠሙትን ችግሮችና ምክንያታቸውን ሊገልፁ ይችላሉ፡፡
3. ቀደም ሲል ተፈላጊውን መረጃ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ወይም ልዩ ተልዕኮ ለተሰጠው ለተገቢው የድርጅቱ አካል በዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ ሀገራት ቀርቦ ከሆነ እንደገና ዝርዝር ዘገባ ማቅረብ ሳያስፈልግ ይህንኑ በትክክል መጥቀስ በቂ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 18

የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ጉዳዮች ምክር ቤት ሰብአዊ መብቶችና መሰረታዊ ነፃነቶችን በሚመለከት በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ቻርተር በተሰጡት ኃላፊነቶች መሰረት ልዩ ተልዕኮ ከተሰጣቸው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አካላት የዚህን ቃል ኪዳን ድንጋጌዎች በማስፈፀም በኩል ስለተገኙት ውጤቶች በኃላፊነታቸው ክልል ዘገባ እንዲያቀርቡለት ሁኔታዎችን ሊያመቻች ይችላል፡፡ እነዚህ ዘገባዎችም የድርጅቶቹ አካላት በአፈፃፀም ረገድ ያደረጓቸውን ውሳኔዎችና ያቀረቧቸውን ሃሳቦች ዝርዝር ሊያካትቱ ይችላሉ፡፡

## አንቀጽ 19

የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ጉዳዮች ምክር ቤት በአንቀጽ 16 እና 17 መሰረት ሀገራት ያቀረቡለትንና በአንቀጽ 18 መሰረት ልዩ ተልዕኮ ከተሰጣቸው አካላት የቀረቡለትን ሰብአዊ መብቶችን የሚመለከቱ ዘገባዎች ለጥናት፣ ለውሳኔና እንደየሁኔታው ለመረጃ እንዲያገለግለው ለሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ሊያስተላልፍለት ይችላል፡፡

## አንቀጽ 20

የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ ሀገራትና የሚመለከታቸው ልዩ ተልዕኮ የተሰጣቸው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አካላት በአንቀጽ 19 መሰረት በሚቀርብ ማናቸውም የውሳኔ ሃሳብ ወይም በሰብአዊ መብት ኮሚሽን በሚቀርብ ሰነድ ወይም በሰነዱ በተመለከተ ጉዳይ ላይ አስተያየታቸውን ለኢኮኖሚና ማኅበራዊ ጉዳዮች ምክር ቤት ማቅረብ ይችላሉ፡፡

## አንቀጽ 21

የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ጉዳዮች ምክር ቤቱ በቃል ኪዳኑ የተገለፁትን መብቶች በማስከበር ረገድ የተወሰዱ እርምጃዎችን እና የተገኙ ውጤቶችን በተመለከተ አጠቃላይ ዘገባዎችንና የውሳኔ ሃሳቦች እንዲሁም በዚህ ረገድ ከአባል ሀገራትና ልዩ ተልዕኮ ከተሰጣቸው አካላት የሚቀርቡለትን መረጃዎች በማጠናቀር ለጠቅላላ ጉባኤው በየጊዜው መግለጫ ያቀርባል፡፡

## አንቀጽ 22

የቃል ኪዳኑን ድንጋጌዎች በማስከበር ረገድ ባላቸው የስልጣን ክልል ውስጥ ተገቢ የሆኑ እርምጃዎች ለመውሰድ ይችሉ ዘንድ፤ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ጉዳዮች ምክር ቤት በዚህ የቃል ኪዳኑ ክፍል መሰረት የሚቀርቡለትን ዘገባዎች ወይም ዘገባዎቹ ካካተቷቸው ጉዳዮች ተገቢ የሆኑትን ፍሬ ነገሮች ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሌሎች አካላትና ለእነርሱ ተጠሪ ለሆኑ ክፍሎች እንዲሁም ቴክኒካዊ ድጋፍ በመስጠት ረገድ ልዩ ተልዕኮ የተሰጣቸው አካላት እንዲያውቋቸው ሊያደርግ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 23

የዚህ ቃል ኪዳን አባል ሀገራት በዚህ ቃል ኪዳን ውስጥ ዕውቅና ያገኙትን መብቶች ለማስከበር የሚደረግ ዓለም አቀፍ እንቅስቃሴ፣ ቃል ኪዳኖችን መፈፀም፣ የውሳኔ ሃሳቦችን መቀበል፣ የቴክኒክ ዕርዳታ ማቅረብ፣ ከሚመለከተው ሀገር ጋር በመተባበር ለምክክርና ለጥናት የሚደረጉ አካባቢያዊ ቴክኒካዊ ስብሰባዎችን ማካሄድና የመሳሰሉትን እንደሚችሉ ተስማምተዋል፡፡

## አንቀጽ 24

የዚህ ቃል ኪዳን ማንኛውም ድንጋጌ በቃል ኪዳኑ የተገለፁትን ጉዳዮች በተመለከተ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ቻርተር ወይም ልዩ ተልዕኮ የተሰጣቸው አካላቱ በተቋቋሙባቸው ደንቦች ውስጥ የሚገኙትን የአካላቱን ተግባርና ኃላፊነት የሚወስኑ ድንጋጌዎችን እንደሚያፋልስ ሆኖ አይተረጎምም፡፡

## አንቀጽ 25

ማንኛውም የዚህ ቃል ኪዳን ድንጋጌ ማንኛውም ሕዝብ የተፈጥሮ ሀብቱን በሙሉና በነፃ ለመጠቀም ያለውን ተፈጥሯዊ መብት እንደሚገድብ ተደርጎ አይተረጎምም፡፡

# ክፍል አምስት

## አንቀጽ 26

1. ይህ ቃል ኪዳን ለማንኛውም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አባል ሀገር ወይም ልዩ ተልዕኮ የተሰጣቸው አካላት አባል ሀገር፣ የዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት መተዳደሪያ ሕግን ለተቀበለ ሀገር፣

በተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ የዚህ ቃል ኪዳን ፈራሚ እንዲሆን ለተጋበዘ ሀገር ለፊርማ ክፍት ነው፡፡

2. ይህ ቃል ኪዳን በየሀገሩ የሕግ አውጪ አካል ፀድቆ ተቀባይነት ማግኘት አለበት፡፡ ቃል ኪዳኑ የፀደቀበት ማረጋገጫ ሰነድ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ መቅረብ አለበት፡፡
3. ይህ ቃል ኪዳን በዚህ አንቀጽ ቁጥር 1 ውስጥ ለተጠቀሱት ሀገራት እንዲቀበሉት ክፍት ይሆናል፡፡
4. የሀገራት መቀበል የሚረጋገጠው የመቀበያ ሰነዱን በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ ዘንድ በማኖር ነው፡፡
5. የተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ ይህን ቃል ኪዳን ለፈረሙ ወይም ለተቀበሉ ሀገራት የማፅደቂያ ወይም የስምምነት ማረጋገጫ ሰነዶችን መረከቡን ያስታውቃቸዋል፡፡

## አንቀጽ 27

1. ይህ ቃል ኪዳን ሰላሳ አምስተኛው የማፅደቂያ ወይም የመቀበያ ሰነድ ለተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ ከቀረበበት ከሦስት ወራት በኋላ የፀና ይሆናል፡፡
2. ሰላሳ አምስተኛው የማፅደቂያ ወይም የመቀበያ ሰነድ ከቀረበ በኋላ ይህንን ቃል ኪዳን ያፀደቀ ወይም የተቀበለ እያንዳንዱ ሀገር የራሱን የማፅደቂያ ወይም የመቀበያ ማረጋገጫ ሰነድ ካስረከበበት ከሦስት ወራት በኋላ ቃል ኪዳኑ በአገሩ የፀና ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 28

ፌዴራላዊ አስተዳደር ባላቸው ሀገራት የዚህ ቃል ኪዳን ድንጋጌዎች በሁሉም የአስተዳደር ክልሎች ያለምንም ገደብ ወይም ልዩነት ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ 29

1. ማንኛውም የዚህ ቃል ኪዳን አባል ሀገር የማሻሻያ ሃሳብ ለተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ ማቅረብ እና ይኸው ሃሳብም በጸሐፊው ዘንድ እንዲቀመጥለት ማድረግ ይችላል፡፡ ዋና ጸሐፊውም የቀረበለትን የማሻሻያ ሃሳብ ለሌሎች ቃል ኪዳኑን ለተቀበሉ ሀገራት በማስታወቅ የቀረበው ማሻሻያ ላይ ለመወያየትና ድምፅ ለመስጠት አገሮቹ ጉባዔ እንዲካሄድ መፈለግ አለመፈለጋቸውን እንዲገልፁለት ይጠይቃል፡፡ ቃል ኪዳኑን ከተቀበሉት ሀገራት አንድ ሦስተኛው የጉባዔውን መካሄድ የሚፈልጉ ከሆነ ዋና ጸሐፊው ጉባዔውን በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አማካይነት ጉባዔው እንዲካሄድ ያደርጋል፡፡ በጉባዔው የተገኙት ድምፅ የሰጡት ፈራሚ ሀገራት

ማሻሻያውን በአብላጫ ድምፅ ከተቀበሉ ማሻሻያው እንዲፀድቅ ለተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ ይቀርባል፡፡

2. የቃል ኪዳኑ ማሻሻያ ሃሳብ የፀና የሚሆነው በተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ ሲፀድቅና ቃል ኪዳኑን የተቀበሉት ሀገራት ሁለት ሦስተኛው በአብላጫ ድምፅ እንደየሀገራቸው የሕግ አወጣጥ ሥርዓት ሲቀበሉት ነው፡፡
3. ማሻሻያው ከፀና በኋላ ቃል ኪዳኑን በተቀበሉት ሀገራት ውስጥ የሕግ ኃይል ይኖረዋል፡፡ እንዲሁም በሌሎቹ ፈራሚ ሀገራት ውስጥ ከዚህ ማሻሻያ በፊት የነበሩት የዚህ ቃል ኪዳን ድንጋጌዎችና እነሱ የተስማሙባቸው የቀድሞ ማሻሻያዎች የፀኑ ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ 30

በአንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 5 የተገለፁት ማስገንዘቢያዎች ቢኖሩም በዚያው አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1 ለተጠቀሱት ሀገራት የድርጅቱ ዋና ጸሐፊ ስለሚከተሉት ዝርዝር ያስታውቃል፤

ሀ/ በአንቀጽ 26 ስለተጠቀሱት ፊርማዎች፣ ማፅደቂያዎችና መቀበያዎች፤

ለ/ በአንቀጽ 27 መሰረት ይህ ቃል ኪዳን የፀናበትን ጊዜና በአንቀጽ 29 መሰረት ማሻሻያዎቹ የፀኑበትን ጊዜ፤

## አንቀጽ 31

1. የዚህ ቃል ኪዳን ቅጅዎች በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት መዝገብ ቤት ይቀመጣል፤ የቻይንኛ፣ የእንግሊዝኛ፣ የፈረንሳይኛ፣ የሩሲኛና የስፓንኛ ቋንቋ ሁሉም ቅጅዎች እኩል እውቅና አላቸው፡፡
2. የተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ ትክክለኛነታቸው የተረጋገጠውን የዚህ ቃል ኪዳን ቅጂዎች በአንቀጽ 26 ለተጠቀሱት ተዋዋይ ሀገራት ያስተላልፋል፡፡